# ወትሮም አልነበረም

እንቧይ ሎሚ መስሎ ፣ ማሳቱ ባይቀርም
የጊዜ ጉዳይ ነው ፣ መቼም ውሎ አያድርም
ሰውን እንዳሞኘ ፣ ዝንተ ዓለም አይኖርም
እባብ ፣ ክንፍ አውጥቶ ፣ እርግብ ሆኖ አይበርም ።

ቅን አሳቢ ሁሌም ፣ ዝንብ ፣ ማርን ላትሰጥ
የማይሆን ይሆናል ፣ ብሎ በመቋመጥ
ዝንቧን ፣ ንብ ይላታል ፣ ጭራሽ ሳትለወጥ
በሂደት እንዳያይ ፣ አርፎ እንዳይቀመጥ ።

ጥሩ አጀማመር ነው ፣ ብለን ሳንጨርሰው
በሶስተኛው ሳምንት ፣ እድገቱ ታወሰው
የተፋውን እምነት ፣ ተመልሶ ላሰው
ጌታው አቶ አብይ ፣ ናደና አፈረሰው
እንዴት እንደ እስስት ፣ ይለዋወጣል ሰው ።

ሚኒሊክ ፣ ኢትዮጵያን ፣ ትላንት አሞግሶ
ይሆናል ፣ ያልነው ሰው ፣ ዋልታና ምሰሶ
የፃፈበት ቀለም ፣ ሳይደርቅ ጨርሶ
ውሎ እንኳን ሳያድር ፣ ባንዴ ተቀልብሶ
አፈር ድሜ አበላው ፣ በጭቃ ለውሶ ።

መልኩን አሳምሮ ፣ ፊደሉን ቀምሮ
ብዙ እንዳላወራ ፣ የሚጥም ለጆሮ
እሹ እንዳልተባለ ፣ ወዲያው ፣ ሳይውል አድሮ
እንደ ጴጥሮስ እንኳን ፣ ሶስቴ ፣ ሳይጮህ ዶሮ
ክህደት አዘነበ ፣ የቀኝ ኋላ ዞሮ
በግ በግ ፣ የሸተተን ፣ ነበረ ቀበሮ
ጭምብሉን አውልቆ ፣ መጣ ተቀይሮ ።

በነ አዜብ ጎላ ፣ በመለስ ግልምጫ
በበረከት ስምዖን ፣ በናርከበ እርግጫ
በነ ስዩም መስፍን ፣ በነ ስብሃት ጡጫ
ተኮትኩቶ ያደገ ፣ በባንዳ ቁንጥጫ
ወትሮም አልነበረም ፣ የህዝባችን ምርጫ
ግምኛ የሚሸት ፣ የሚቆርጥ አፍንጫ ።

ታዛቢው
**April 13, 2018**